# ኢትዮጵያዊቷ አሪታ ፍራንክሊን!

**በዘነበ በቀለ**

ርዕሱ ብዙዎችን ያሳስታል ብዬ አልገምትም። የሁለቱንም ዘፋኞች ሙዚቃ አገናዝቦ መረዳት የሚቻል ነውና። አሪታ በልጅነት ዘመኗ "ሬሰኩዩሚ" እያለች ያቀነቀነችው ሙዚቃ በአንድ በኩል የሙዚቃው ርዕስ ጭንቀቷን ገላጭ ቢመስልም በሌላ በኩል ደግሞ የድምፁዋን ልክ ያሳየችበት እፁብ ድንቅ የሆነ ዜማዋ ነው። ኢትዮጵያዊቷ አሪታ ፍራንክሊን ደግሞ በባህላዊ መንገድ ችግርን አምቆ መያዝ እንጂ ለአደባባይ አስጥቶ ማሳየት የተለመደ አይደለምና ሁሉን ቻይ ሆና መከራዋን የምትገፋው ድምፃዊቷ ማሪቱ ለገሰ ነች። ማሪቱ ከአሪታ ጋር የምትመሳሰልበትና የምትለያይበት ጉዳይ አለ። የምትመሳሰለው በድምፅ ገደቧ ማለትም የሶፕራኖ ድምፅን ገደብ ሙሉ በሙሉ አጠናቃ የምትጫወት መሆኗ ሲሆን የምትለያየው ደግሞ አድኑኝ በማለት እንደ ማሪታ አለመጠየቋ ነው። ማሪቱ በሀገራችን ውስጥ የሶፕራኑ ድምፅ ገደብን ጠብቃ የምታቀነቅን ምንም አይነት የፎልሴቶ አዘማመር ጠባይን የማትከተል በይበልጥም የጉሮሮ አዘማመር ባህርይን የያዘች ብቸኛ ዘማሪ ነች። ከሷ ጋር ተመሳሳይ አዘማመር ባህርይ የምትከተለው ብዙነሽ በቀለ ስትሆን የዜማ ስኬል ገደባቸው አንድ ቢሆንም ባሰራር ቴክኒክ ይለያያሉ። ብዙነሽ የመተላለፊያ ዜማዎችን በትናጋ፤ በራስና በላንቃ አዘማመር ፈሊጥ አስቸጋሪውን ቦታ ስታልፈው ማሪቱ ግን ልክ እንደ አሪታ ፍራንክሊን ፊት ለፊት ተጋፍጣ ድምፅ የምትፈጥረው ያለምንም ቮይስ ማስክ መሆኑ በ"አምባሰል" ሙዚቃዋ ላይ ይንፀባረቃል። ማሪቱ የባህል መገለጫ ናትና አምባሰልን ስትዘምር በትክክለኛ ቶንና ስሜት ነው። ያም የሆነው አምባሰል ቅኝት የሚቃኘው በብሩህ ተስፋ አመላካችነት ስሜት ላይ በመሆኑ የማሪቱ ድምፅ ከርቀት ሆኖ የሚጣራ የተስፋ ምልክት ድምፅ ነው። ከዚህ ሌላ ቃላቶቿ ግልፅና ተደማጭ መሆናቸው ከአሪታ ጋር ያመሳስላታል።

ያለመታደል ሆኖ በሀገራችን ውስጥ የተፈጠሩ የሙያው ሰዎች ምንም ጊዜ በሙያቸው ተጠቅመውበት አያውቁም። ነፍሱን ይማረውና ታዋቂው አርቲስት ጥላሁን ገሰሰ የልጅነት ዘመኑን በሙሉ ሰውን በማዝናናት ሲያሳልፍ ለህይወቱ የሚበጀው ሀብት አልሰበሰበም ነበር። ታምራት ሞላ፤ አለማየሁ እሸቴ፤ መልካሙ ተበጀ ሙሉቀን መለሰ ወዘተ በህይወታቸው ገንዘብ ለማበጀት አልሮጡም። ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ስጦታ ያላቸው አርቲስቶች በትምህርት ዕውቀታቸውን የገነቡ አርቲስቶች ሁሉም አይነት አሏት። ነገር ግን አንዳቸውም በሙያቸው ተጠቃሚ ሆነው አያውቁም። ለምን እንዲህ ሆነ? ብሎ መጠየቅ ይቻል ይሆናል፤ ገንዘብ ባለመፈለጋቸው? ሁኔታው ስላልተፈጠረላቸው? መልስ ለመስጠት የራሱ ጥናት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። አንዳቸውም ተጠቃሚ አለመሆናቸው ግን ያለ ሀቅ ነው። ሻለቃ ሳህሌ ደጋጎን ያህል አቀናባሪ የትም ተጥሎ የሽምግልና ዘመኑን በችግር እየገፋ እንደነበር ተገልፆአል። በሀይሉ እሸቴ በህመም ሲሰቃይ ነበር ሲባል ሰምተናል። ታላቁ ደራሲ ተስፋዬ ለማንስ ከምን ላይ እንደሆን የሚያውቅ አለ? ጌታቸው ካሳስ? አረ ስንቱ!

ይህ የሆነበት ምክንያት ታላላቅ የሙያው ጠበቆች እንደ ፕሮፌሰር አሸናፊ ከበደ አይነቶቹ ባለመታደል ለሀገራቸው መሬት ሳይበቁ ያለፉ ናቸው። ሆኖም ግን በኖሩበት ዘመን ሁሉ የሙዚቃን ደረጃ ከፍ ለማድረግ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ያ! ጥረት ሰምሮ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማህበር ቢገፋት የማይነቃነቅ ሙያዊ ማህበር በሆነ ነበር። ያለ ሙያ ማህበር ድግሞ መብትን ማስከበር የሚታሰብ አይሆንም። ውጤቱ ለአንዳንድ አጭበርባሪዎች ሲሳይ ሆኖ መሰንበት ነው። በመጨረሻም ለህመሙም ሆነ ለእርጅናው ዘመን የሚደርስለት ለአርቲስቱ ሁሉ የራሱ እንጉርጉሮ ሆኗል። ሙዚቀኛ የህዝብን ጭንቀት ተጋሪ በመሆኑ፤ ከህዝብ ጭንቀትን ከሀገር ባህልን ይወርሳል። ስለሆነም በበሽታ የመጠመጃው ዕድል ከፍተኛ ነው። ልክ እንደማሪቱ በተፈጥሮ ፀጋቸው ያለምንም ፎርማል የድምፅ ልምምድ ተፈላጊው እርከን ላይ የደረሱ ጥቂት አይደሉም። አሪታ

ፍራንክሊን በቤተክርስቲያን ዘማሪነት ያዘማመር ፊሊጥን አውቃለች። የኛዎቹ ለማ ገብረህይወትና ማሪቱ ለገሰ ከከፍተኛው የድምፅ አወጣጥ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው። ግን አስተማሪያቸው ምናልባትም ለማሪቱ የጦሳ ተራራ ለለማ ገ.ህይወትም የቡልጋ ተራራ ሊሆን ይችላል። በገደል ማሚቱነት የተባበራቸው "reciprocal" በሆነ አቀራረብ የተባበራቸው። በሀገራችን ሙዚቃ ላይ የየራሳቸውን ስታይል ትተው ያለፉም ያሉም ሙዚቀኞች በርካታ ናቸው። ለምሳሌም ያህል፦ ማሪቱ ለገሰ፤ ብዙነሽ በቀለና ለማ ገብረህይወት የሶል ሙዚቃ ስታይል፦ ዓለማየሁ እሸቴ "ኢትዮ ሮክንሮል" ፤ ጌጡ አየለ፤ መልካሙ ተበጀ፤ ትዕግስት ፋንታሁንና አበባ ደሳለኝ፤ "ካባሬት ሙዚቃ"፤ ባህታ ገ.ህይወት፤ ሙሉቀን መለሰና አስቴር አወቀ "ሪዝም ኤን ብሉስ"፤ እማሆይ ፅጌ ማርያም ገብሩ "ኢትዮ ክላሲካል ፒያኖ" በተለይም የሜንዶልሰንና የሹበርትን አጨዋወት ስልት የተከተለ፤ አሸናፊ ከበደ "ሲምፎኒክ ፖየም" ለፍሉትና ለስትሪንግ መሳሪያዎች፤ ነርሲስ ናልባንዲያን ኳየር፤ ከዚህ ሌላ በየጨዋታዎቹ ላይ የየራሳቸውን ችሎታ ያበረከቱ በርካታ ናቸው ለመጥቀስ ያህል ጌታ መሳይ አበበ በትዝታ ላይ፤ ጌታቸው ካሳና በዛ ወርቅ በትዝታ ላይ፤ የግጥም አጠቃቀምን ከባህላዊው የወል ግጥም ስሪት ወጣ ባለ መልኩ አዲስ ስታይል በማቅረብ ያበረከቱ ደግሞ ንዋይ ደበበ፤ ቴዲ አፍሮ፤ ጎሳዬ ተስፋዬ፤ ፍቅር አዲስና ትዕግስት በቀለ፤ ሲሆኑ፤ ተሾመ ምትኩ፤ መልካሙ ተበጀና ፍሬው ሀይሉ ትሩባዱር ስታይልን በማስተዋወቅ፤ ወዘተ ይገኙበታል። ጥላሁን ገሰሰ፤ ታምራት ሞላ፤ መሃሙድ አህመድና ዓለማየሁ እሸቴ በሶል፤ በጃዝ፤ በሪዝም ኤን-ብሉስ እና በሮክንሮል ውስጥ በርካታ ጨዋታዎች አሏቸው።

ባጠቃላይ ሙያቸው ሌላውን እንጂ እራሳቸውን ያልጠቀመ በህይወት ያሉና ያለፉ በርካታ የሙያው ሰዎች መኖራቸው የማይታበል ነው። ካሳ ተሰማ ክራሩን በየሄደበት ከተጫወተ በሁዋላ ይሰብር ነበር። ሲጠየቅም እኔ ቧምቧ ሰሪ እንጂ ሙዚቀኛ አይደለሁም የሚል መልስ ነበር የሚሰጠው። ብስጭቱ ምን እንደሆን ግን ሳይታወቅለት ነው ያለፈው። አስናቀች ወርቁ በክራር፤ አሰፋ አባተ በመሰንቆ፤ የመጀመሪያውን ያገር ባህል ኦርኬስትራ የመራው እዩኤል ዮሀንስ በድርሰትና በዝማሬ። መዲናና ዘለሰኛ ይጥና ታደገኝና አለማየሁ ፋንታ፤ ገረርሶ ወሰኑ ዲዶ በመሰንቆ፤ አርጋው በዳሶ በዝማሬ፤ በኦሮሞኛና በአማርኛ አቀላጥፎ የሚጫወተው አበበ ተሰማ በዋሽንት መለኩ ገላውና አፈወርቅ ወደር አይገኝላቸውም። ሁሉም ለዚህ ሙያ ከፍተኛ አሰተዋፅኦ ያበረከቱ የሙያው ሰዎች ነበሩ / ናቸው። በሙያቸው ተጠቅመውበታል? አይመስለኝም። የሙዚቃ ጥበባቸውን እንደዘሩ ሳይሰበስቡት ያለፉም በህይወት ያሉም አሉ። ይህ ችግር በቀጣይነት የሚዘልቅ ለመሆኑ አሁንም ያለው የሙያው ሰዎች አለመሰባሰብ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ስለዚህም ስቶክሆልም የተቋቋመው የኢትዮጵያ ሙዚቃና ድራማ ግሩፕ ሁሉም በያለበት ተደራጅቶ የጋራ አለም አቀፍ የሙዚቃ ማህበር እንዲመሰረት ጥሪውን ያቀርባል። ተመሳሳይ ግንዛቤ ካለዎት አስተያየትዎን በሚቀጥለው አድራሻ ያድርሱን።

www.kitabethiopia.com

(የኢትዮጵያ ሙዚቃና ድራማ ግሩፕ)